# 33ኛውን የህወሓት የልደት በዓል በማስመልከት ከህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት የተሰጠ መግለጫ

የትግራይ ህዝብ ተጭኖበት የነበረውን የጭቆና ቀንበር በአስደናቂ ዕናት አስወግዶ ልማት፣ ዴሞክራሲና ሰላም የሰፈነባት፤ በፍላጎትና በእኩልነት ላይ የተመሰረተች አንዲት አገር ለመገንባት የካቲት 11/1967 ዓ.ም. በድርጅቱ በህወሓት እየተመራ ያቀጣጠለው ትግል እነሆ 33 ዓመታት አስቆጥሯል። የህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ ለመላው የትግራይ ህዝብ፣ ለታጋዮችና ለአባላት፣ ለኢህአዴግ አባል ድርጅቶችና ለአጋር ድርጅቶች እንዲሁም ለትግራይ ህዝብ ትግል ወዳጅ ህዝቦች እንኳን የትግራይ ህዝብ የትጥቅ ትግል ለተጀመረበትና ለህወሓት የልደት ቀን የካቲት 11 በሰላም አደረሳችሁ ይላል።

የተከበራችሁ የትግራይ ህዝብና የህወሓት አባላት!

መስመራችንን አጥርተን የልማት፣ የዴሞክራሲና የሰላም ጉዟችንን ለማጠናከር የለኮስነው የተሃድሶ እንቅስቃሴያችን እነሆ 7ኛ ዓመቱን አስቆጥሯል። በዚህ እንቅስቃሴ የጠራ መስመራችን፣ የቀየስናቸው ስትራተጅዎችና ፖሊሲዎች ተግባር ላይ ውለው የህወሓትና የኢህአዴግ አባላት፣ የትግራይ ህዝብና የኢትዮጵያ ህዝቦች ስለታገሉላቸው የልማትና የዴሞክራሲ ፍሬ ማፍራት ጀምረዋል። ከጠራ መስመራችን የሚመነጩት ስትራተጅዎቻችን፣ ፖሊሲዎቻችንና ዕቅዶቻችን በተግባር ላይ ውለው ሰፊ የዴሞክራሲ፣ የልማትና የሰላም ህዝባዊ እንቅስቃሴ ማዕበል ሊፈጥሩ እንደሚችሉ ማንም ሊክደው የማይችል ሓቅ ሆኗል።

ባለፉት ስርዓቶች ወይም ባለፈው ታሪካችን ታይቶ በማይታወቅ ፍጥነት ለአምስት ዓመታት በተከታታይ ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት አስመዝግበናል። በዴሞክራሲና በመልካም አስተዳደር መስክም አዎንታዊ ለውጦች እያስመዘገብን ዴሞክራሲያችን በፅኑ መሠረት ላይ መመስረት የሚችልበትን ሰፊ ልምድ

እየሰነቅን ወደፊት በመራመድ ላይ እንገኛለን። ህዝባችን ብሩህ ተስፋ እያየ አዲስ ራዕይ ሰንቆ ወደ አዲሱ ሚሌኒየም ተሸጋግሯል። ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ስርዓታችንን በመሰረቱ በመለወጥ ይበልጥ ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ በምናደርግበት እንዲሁም የአገራችንን ህዳሴ በምናረጋግጥበት መድረክ ላይ ቆመናል። ለ33ኛ ጊዜ የምናከብረው የየካቲት 11 በዓልን ልዩ የሚያደርጉት ባህሪያትም እነዚህ ናቸው።

ያለንበትን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ስርዓት ወደ ተሟላ ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በመሰረቱ ለመለወጥ ወሳኝ እርምጃዎችን ተራምደናል ለማለት ብንችልም እንኳ የተወሳሰበውና ጠመዝማዛው ቀጣይ ጉዟችን ግን ተገባዷል የሚባል አይደለም። ዋነኛ ጠላታችን የሆነውን ድህነትን ገና አላጠፋነውም። ድህነትን አሸንፈን የማይቀለበስ ልማትንና አቅምን ሙሉ በሙሉ እስከምንገነባ ድረስ ፀረ-ልማትና ፀረ-ዴሞክራሲ አመለካከቶችና ተግባራት የሚፈታተኑን መሆናቸውን በተሃድሶ መስመሮቻችን ግልፅ አድርገናል። ሊያጋጥሙ የሚችሉ ውስብስብ ጉዳዮችንና አደጋዎችን መለየት ብቻ ሳይሆን ወዳስቀመጥነው ራዕይ እስከምንደርስ ቀጣይ ትግል እንደሚኖርብንና እንዴት ልንታገል እንደሚገባን መታገያ ትጥቅ ይዘናል።

## የተከበራችሁ የትግራይ ህዝብና የህወሓት አባላት!

የጀመርነው ድህነትን የማጥፋት፣ የልማት፣ የዴሞክራሲ፣ የመልካም አስተዳደርና ሰላምን የማረጋገጥ ጉዟችን ሳያቋርጥና በፍጥነት እንዲራመድ፣ የየካቲትንና የሰማዕታትን አደራ አንግበን በፅናትና በታታሪነት የጀመርነውን ትግል አጠናክረን እንድንቀጥል የህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ ጥሪውን ያቀርባል። ሁላችንም የምናየው ብሩህ ተስፋ እንዲደምቅ፣ ድህነት ጠፍቶ ልማት፣ ዴሞክራሲ፣ መልካም አስተዳደርና ሰላም እንዲረጋገጥ የምታደርጉትን አኩሪ ተጋድሎ የህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ በዚህ አጋጣሚ ለማሞገስ ይወዳል።

## የተከበራችሁ የህወሓት አባላት!

ልማት፣ ዴሞክራሲ፣ መልካም አስተዳደርና ሰላም እንዲረጋገጥ የአባላት መሪ ሚና መተኪያ እንደሌለው የህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ በፅናት ያምናል። ስርዓታችን በተሟላ መንገድ አብዮታዊ፣ ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን ግንባር ቀደምና የተግባር መሪዎች ሆናችሁ የምታከናውኑትን ተግባርና የምታስመዘግቧቸውን ድሎች የህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ ብቻ ሳይሆን ህዝባችንም የሚገነዘበው ሃቅ ነው። እስከ አሁን ያስመዘገብናቸውን ድሎች ጠብቀን የጎደሉትን አሟልተን ተደራጀተውም ሆነ ሳይደራጁ ድሎቻችን ለመንጠቅ የሚያልሙ ጠላቶቻችንን እያሳፈርን ለህዝባችን ደህንነትና ዕድገት በፅናትና በታታሪነት ወደፊት እንድንራመድ በየካቲት ስም ጥሪያችንን በድጋሚ እናቀርባለን።

## የተከበራችሁ የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች!

በእኩልነት ላይ ለተመሰረተ የኢትዮጵያ ህዝቦች አንድነት ለልማት፣ ለዴሞክራሲና ለአገራችን ሰላም ክንዳችንን አስተባብረን በመታገል የደርግን ፋሽስታዊ ስርዓት አሸንፈናል። ዋነኛ ጠላታችን የሆኑትን ድህነትንና ኋላቀርነትን በተባበረ ክንዳችን እያንበረከክን፣ ፈጣንና ዘላቂነት ያለው የኢኮኖሚ እድገት በአገራችን እያረጋገጥን፣ ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደርን እየገነባን፣ በሚያኮራ ፍጥነት እየገሰገስን እንደምንገኝ ገሃድ ነው። የጀመርነው ፈጣን ልማት ሳይደናቀፍ እንዲቀጥል፣ ዴሞክራሲና መልካም አስተዳደር እንዲያብብ በምናካሂደው ተጋድሎ ከህወሓትና ከትግራይ ህዝብ ጎን ቆማችሁ በጋራና በቀጣይነት እንደጀመርነው እንደምንዘልቅ አያጠራጥርም።

ህወሓት በኢህአዴግ የጋራ ክንድ ውስጥ ሃይሉን አስተባብሮ ድህነትን ለመደምሰስና ልማትና ዴሞክራሲ ተረጋግጦ አገራችን በአዲሱ ሚሌኒየም እንድትታደስ በሚደረገው የጋራ ትግል ውስጥ ከጎናችሁ ሆኖ እንደሚቀጥል በዚህ አጋጣሚ በድጋሚ ሊያረጋግጥላችሁ ይወዳል።

**የተከበራችሁ አጋር ድርጅቶች!**

**የተከበራችሁ የትግራይ ህዝብና የህወሓት ወዳጆችና ደጋፊዎች!**

**የተከበራችሁ የኢትዮጵያ ህዝቦች!**

*አገራችን አንድ አገር ሆና የህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ ያደረጋችሁትንና የምታደርጉትን ትግልና ትብብር ህወሓት ያደንቀዋል፡፡ ድህነት ተደምስሶ፣ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድነት በአገራችን ሰፍኖ፣ ልማትና መልካም አስተዳደር ተረጋግጦ፣ ኢትዮጵያ በአዲሱ ሚሌኒየም ታድሳ የተከበረች አገር እንድትሆን በሚደረገው የጋራ ትግል ውስጥ ህወሓት የየካቲት 11 ቃል ኪዳኑን ዳግም በማደስ ከጎናችሁ በፅናት እንደሚሰለፍ ለማረጋገጥ እንወዳለን፡፡*

**የጀመርነውን ፈጣንና ዘላቂ ልማት ጠብቀን እንቀጥላለን!**

**ዴሞክራሲንና መልካም አስተዳደርን እናጠናክራለን!**

**ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን እንገነባለን!**

**ዘላለማዊ ክብር ለሰማዕታት!**

**የህወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ ጽ/ቤት**

**የካቲት 11/2000 ዓ.ም.**